# የደቡብ አፍሪቃ የነፃነት ጉዞ

**በመድህን የምርምርና የጥናት ክፍል ተዘጋጀ (9/26/2008 ኣ.እ)***

ደቡብ አፍሪካ ለዘመናት በነፃነት የኖረች ሃገር መሆኗን ታሪክ ፀሃፊዎች መዝግበውታል። በነዚህም የነፃነት ዘመናት የሃገሪቷ ነዋሪዎች አፍሪቃውያን ብቻ ነበሩ። በወቅቱ፣ ደቡብ ኣፍሪቃ ኣንድ ወጥ ሃገር ሳትሆን በተለያዩ ባላባቶች የሚገዙ መንግስታት ጥርቅም ነበረች። የውጭ አጥቂ ጠላት ሲመጣ ግን፣ እነዚህ የተለያዩ የባላባት ግዛቶች ኣንድ ላይ በመሆን ኣገራቸውን ከጥፋት ለማዳን ይከላከሉ ነበር። እንዲህ ለዘመናት የተጠበቀው ነፃነት መጀመሪያ የተደፈረው ከ355 አመታት በፊት በ1652 ኣ.እ እንደሆነ ታሪክ ይነግረናል። ይህም ከሆላንድ የተነሱ ኣውሮጳውያን የደቡብ ኣፍሪካን የባህር ጠረፍ ወረው ሁከት የጀመሩበት ዘመን ነበር። ወረራውን ኣስከትለው እነዚህ እስካሁንም «ቦሮች» በሚል ስም የሚጠሩ ኣውሮጳውያን የአፍሪቃውያኑን ከብቶች መዝረፍና መሬታቸውን መቀማት የእለት ተእለት ተግባራቸው ኣደረጉት።

ይህ ወረራ ብዙ ግጭቶችን እስነስቷል። ገሚሱን አፍሪቃውያን ገሚሱን ደግሞ ቦሮች እያሸነፉ ግጭቱ ለሁለት መቶ ስምንት ዓመታት ቀጠለ። ደቡብ አፍሪቃውያንን ከባድ መከራ ውስጥ የጣለው ጦርነት የተካሄደው እንግሊዞች በ1860 ኣ.እ ያካሄዱት ወረራ ነበር። እንግሊዞች ደቡብ አፍሪቃን ሲወሩ ዘመናዊ ጠመንጃዎችን መድፎችንና ፈረሰኞችን በመጠቀማቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በአፍሪቃውያኑ ላይ ከባድ ጉዳት ኣደረሱ። አፍሪቃውያኑም ኣስራ ስምንት ዓመታት በፈጀው ትግል ዘጠኝ ከባድ ጦርነቶችን ካካሄዱ በኋላ በ1878 ኣ.እ ነፃነታቸውን አጡ። እንግሊዞችም በ1900 ኣ.እ የቅኝ ግዛት መንግስት አቋቋሙ።

ከኣስር ዓመታት የእንግሊዝ አገዛዝ ቆይታ በሂላ በ1910 ኣ.እ የቅኝ ግዛቱን መንግስት ለእንግሊዝና ለቦር ሰፋሪዎች ኣስረክበው የተዘዋዋሪ ቅኝ ግዛቱ ሥርዓት ተጀመረ። የኣገሪቱም ስም የተባበሩት የደቡብ አፍሪካ መንግስት ተብሎ ተሰየመ። የተቋቋመው መንግስትም ኣፍሪቃውያንን በሞላ ያገለለ የእንግሊዞችንና የቦሮችን ነፃነትና የበላይነት የሚያረጋግጥ ህግ ለመጀመሪያ ጊዜ ደነገገ። የአፍሪቃውያኑን መብት፣ ነፃነትና ሰብዓዊ ክብር ያለገደብ መድፈር ጀመሩ። የአፍሪቃውያኑ ባህል፣ ወግ፣ ስርኣትና ልምዶች በህግ እንዲጨፈለቁ ተደረጉ።

የአፍሪቃውያኑ ህፃናት የሚማሩባቸው የሚሲዮን ትምህርት ቤቶች ተስፋፉ። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተብየዎች የአፍሪቃውያኑን ዝቅተኛነትና የነጮችን ታላቅነት ያስተምሩ ስለነበረ፣ አፍሪቃዊ ወላጆች ኣማራጭ ቤተ ክርስቲያን መፈለግ ጀመሩ። በወቅቱ በፃነት የቆመች ኣገር ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረች በ1892 ኣ.እ ቤተ ክርስቲያኗ ደቡብ ኣፍሪቃ ውስጥ ተመሰረተች። ይህም ቢሆን የባህል ማጥፋቱ ዘመቻ፣ ነፃነት የመግፈፉ ሂደት እና ኣይን ያወጣ ጭቆና እየባሰ እንጂ እየረገበ ኣልመጣም። ስለዚህ፣ አፍሪቃዊያኑ ይህንን ኣስከፊ ጭቆና ለመቋቋም የሚችሉት በህብረት በመታገል መሆኑን ኣመኑበትና በ1912 ኣ.እ የአፍሪቃ ብሄራዊ ጉባኤን ኣቋቋሙ።

ይህንን ኣገራዊ ገባኤ ካቋቋሙት መሃከል በመጀመሪያ የሚሲዮን ትምህርት ቤት በሂላም በ በኣሜሪካና በእንግሊዝ ኣገር የተማሩት ፒክስሊ ካ ኢስካ ሴሚ (Pixley ka Isaka Seme) ይገኙበታል። ሴሚም የመጀመሪያው የአፍሪቃ ኣህጉራዊ ሁባኤ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ። ሊቀመንበሩም በምረቃ ንግግራቸው የሚቀጥለውን ተናገሩ። «እኛ ደቡብ አፍሪቃውያን ኣንድ ነን፣ በመሃከላችን የሚገኙት

---

*ኣ.እ = ኣመተ እግዚእ = A.D - ይህም በልማድ የፈረንጆች ኣቆጣር የምንለው ነው።
ኣ.ም ወይም በቀድሞው ኣፃፃፍ ዓ.ም = ኣመተ ምህረት - ይህም ኣንዳንድ ሰወች እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር የሚሉት ነው።

መከፋፈልና ቅናት ናቸው፣ የባርነት ማጥ ውስጥ እንድንቦካ የሚያደርጉን፡፡» ጉባኤውም የተመሰረተው የደቡብ አፍሪቃን ታዋቂ ባላባቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች፣ የሃገሪቱን ታዋቂ ምሁራን በማቀፍ ነበር፡፡ ጉባኤውን የሚመሩ ሁለት የመማክርት ሸንጎዎች ተዋቀሩ፡፡ የመጀመሪያው የህግ መወሰኛ የተሰኘ ሲሆን የባላባቶቹን ተወካዮች ያቀፈ ነበር፡፡ ሁለተኛው የህግ መምሪያ ሲሆን፣ ሌሎች ተመራጮችን ያካትታል፡፡ ጉባኤውም፣ የአፍሪቃውያንን ነፃነትና መብት ለማረጋገጥ የተቋቋ እንደሆነ፣ ትግሉንም በሰላማዊ ስልት እንደሚያራምድ አረጋጠ፡፡

የአህጉራዊው ጉባኤ ከመመስረቱ በፊትና እንግሊዞች አገሪቱን ከወረሩ በኋላ ማለትም በ1867 አ.እ እብነ በረድ፣ እንዲሁም በ1886 አ.እ የወርቅ ሃብት በብዛት በአገሪቱ ውስጥ ተገኙ፡፡ በተጨማሪም አብዛኛውን ለም የእርሻ መሬት አውሮጳውያኑ ዘርፈው ይዘውት ስለነበረ የአፍሪቃውያኑን ጉልበት የሚበዘብዙበትን ስርአት መቀየስ ጀመሩ፡፡ አፍሪቃውያኑን ከያዙት መሬት ለመንቀል የሚያስችላቸውን የመሬት ይዞታ ህግ አወጡ፡፡
ይህም ህግ አፍሪቃውያን ይዘውት የነበረውን መሬት እንዲሸጡ፣ ሲሸጡም ለነጮች ብቻ እንዲሸጡ፣ አፍሪቃውያኑም መሬትም ሊኖራቸው የሚችለው በክልላቸው ውስጥ ብቻ እንዲሆን ተብሎ ተደነገገ፡፡

የአፍሪቃውያኑ ክልል ድርቅ የሚያጠቃው ምድር ስለነበረ ችጋርና ረሃብ ተስፋፋ፡፡ በዚህም ምክንያት የሚኖሩበትን ስፍራ እየለቀቁ ፈረንጆች እርሻ ውስጥ እንደዚሁም በማእድን ቆፋሪነት በአስከፊ ሁኔታ እንዲያገለግሉ ሁኔታው አስገደዳቸው፡፡ ቀጥሎም አፍሪቃውያን ሊከፍሉት የማይቻላቸውን እንዲከፍሉ የሚያስገድድ የታክስ ህግ አወጡ፡፡ በዚህም ሳቢያ አፍሪቃውያን ያለ የሌለ ንብረታቸውን እየተው ወደ ከተማዎች፣ ወደ ማእድኖች እና ነጮች ወደያዝዋቸው እርሻዎች መጉረፍ ጀመሩ፡፡ እንዲህም ሆኖ የአፍሪቃውያኑ ባርነት በተጠናከረ መልኩ ቀጠለ፡፡ ለስራ ፍለጋ አፍሪቃውያኑ በየቦታው መበተን ሲጀምሩ ከቦታ ቦታ መዘዋወርን የሚቆጣጠር ህግ ወጣ፡፡ በዚህ ህግ የተነሳም አፍሪቃውያን መታወቂያ ወረቀት እንዲኖራቸው መታወቂያቸውም የሚኖሩበትንና የሚሰሩበትን ስፍራ እንዲያመለከት ተደረገ፡ ፖሊሶችም በምንም ጊዜና ቦታ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ስልጣን ተሰጣቸው፡፡

የአፍሪቃ አህጉራዊ ጉባኤ ይህንን አስከፊ ስርአት በመቃወም በ1919 አ.እ ተንቀሳቀሰ፡፡ የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ያተኮረው ከቦታ ቦታ በነፃ መንቀሳቀሱን በሚገድበው ስርአት ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማእድን ሰራተኞች አስከፊ ሁኔታ በመቃወም በሚደረገው ስራ የማቆም አድማ ላይ ነበር፡፡ አህጉራዊው ጉባኤ እነኝህን ጥሪዎች ማድረጉን አንዳንድ የጉባኤው አመራር አባላት ተቃወሙ፡፡ ምክንያታቸውም «ድርጅቱ ከሚያራምደው ሰላማዊ ትግል የወጣ ነው፡፡» የሚል ነበር፡፡ ያቀረቡትም አማራጭ ስልት፤ መልእክተኞች ወደ እንግሊዝ መንግስት መላክና አቤቱታ ማቅረብን ነበር፡፡ ይህንን ስልት በመከተል በ1914 አ.እ እና በ1919 አ.እ ጥቂር አፍሪቃውያን ወደ እንግሊዝ ተላኩ፡፡ ከእንግሊዝ መንግስት የተሰጣቸው መልስ ግን «ይህ የደቡብ አፍሪቃ የውስጥ ጉዳይ ስለሆነ የእንግሊዝ መንግስት አያገባውም፡፡» የሚል ነበር፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ አህጉራዊ ጉባኤ አመራር ሊሰጥ ባለመቻሉ የተቀየሙ አካላት፣ ትግሉን ለማራመድ ይቻል ዘንድ ሌሎች ድርጅቶችን አቋቋሙ፡፡ በዚህም መሰረት በ1921 አ.እ አለም አቀፍ ሶሻሊስት ድርጅት እንዲሁም በ1919 አ.እ የንግድና የኢንዱስትሪ ሰራተኞች ህብረት ተቋቋሙ፡፡ የተለያዩ አካላት ቢቋቋሙም የዘረኛው የነጮች መንግስት ጭቆና፣ አፈና እና ግድያ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ የስራ አይነትን ከጎሳዎች ጋር የሚያጣምር ህግ ወጣ፡፡ በዚህ ህግ የተነሳም «አፍሪቃውያን የማሰብ ችሎታ የሌላቸው እንስሳዎች ናቸው፡፡» የሚለው አስተሳሰብ ስለከሰነ፣ ከጉልበት ስራ ውጭ ሌላ ስራ እንዳይሰሩ በህግ ተደነገገ፡፡ ይህንን እንሰሳዊ ችሎታቸውን በስራ መተርጎም እንዲችሉ ትምህርታቸው ከ3ኛ ከበዛም ከ6ኛ ክፍል እንዳያልፍ የሚገድብ ህግ ወጣ፡፡ የአፍሪቃውያን አሰቃቂ ኑሮ እየተጠናከረ ቢሄድም የአፍሪቃ አህጉራዊ ኮሚቴ ተመጣጣኝ እንቅስቃሴ መወጠንና መምራት ተሳነው፡፡ በህዝብ ግፊትም የተነሳ ጉባኤው የአመራር ለውጥ እንዲያደርግ ተገደደ፡፡ ተከታትሎም ጄ-ቴ ጉሜዲ (J.T. Gumede) የጉባኤው ሊቀመንበር እንዲሆኑ በ1927 አ.እ ተመረጡ፡፡ ጉሜዲም በጉባኤው ላይ ነፍስ

ለመዝራትና ለማንቀሳቀስ ሞከሩ። ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ማለትም ከደቡብ አፍሪቃ ኮሚኒስቶች ጋር ተባብሮ ለመስራት ሞከሩ። ይህም ያስቆጣቸው የጉባኤው አመራር አባላት በ1930 ኢ.አ ሊቀመንበሩን አስወገዷቸው። ከዚያ በሗላ ለአስር አመታት ጉባኤው የረባ እንቅስቃሴዎችን አላካሄደም።

በድርጅቱ መዳከምና በአንፃሩም የነጮች ጭቆና መክረር፣ የተለያዩ አዳዲስ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ምክንያት ሆነ። በ1947 ኢ.አ የህንዶችና የክልሶች ማህበራት ተቋቋሙ። እነኚህና ሌሎችም ድርጅቶች ከጉባኤው ጋር ተባብረው ለመስራት ተስማሙ። የስምምነት ሰነዶችንም ተፈራረሙ። ይህም ሆኖ ጉባኤው የሚያደርጋቸው አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ከአውሮጳውያን ጭቆና ጋር ባለመመጣጠኑ የተበሳጩ ወጣቶች የሸንጎውን ወጣት ክንፍ በ1944 ኢ.አ. አቋቋሙ። ይህንን ክንፍ ካቋቋሙት ታዋቂ ሰዎች ኔልሰን ማንዴላ (Nelson Mandela)፣ ዎልተር ሲሱሉ (Walter Sisulu)፣ እንዲሁም ኦሊቨር ታምቦ (Oliver Tambo) ይገኙበታል። የወጣቱ ክንፍ እምነት አፍሪቃውያን ነፃነታቸውን ሊያገኙ የሚችሉት በራሳቸው ትግል ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ሰፊውን ህዝብ የመራራው ትግል አካል እንዲሆን ማደራጀትና ትግሉ ለሱ መሆኑን እንዲረዳ ማድረግ ማስፈለጉን፤ እንዲሁም ነጋዴውን በየዘርፉ፣ ሰራተኛውን በየመልኩ የሚያንቀሳቅሱ አካላት ማቋቋም ነበር። የጉባኤው ወጣት ክንፍም እንቅስቃሴውን ለማጠናከር የሚረዱ እንደ ስራ ማቆም፣ ስራ ማቀዝቀዝ፣ በዘረኛው መንግስት የወጡ ህጎችን መጣስ እና የመሳሰሉትን እቅዶች ለጉባኤው አመራር አቅርበው በስራ እንዲገለፁ ተፈቀደላቸው። የሸንጎው ወጣት ክንፍ ከተቋቋመ በሗላም ማለትም 1950 ኢ.አ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ሸንጎውም ሌሎች ድርጅቶችንና ሰፊውን ህዝብ ያቀፉ እንቅስቃሴዎችን በስራ መተርጎም ጀመረ። ሸንጎው ያተኮረባቸው ህጎች ቅደም ተከተል፤ በመጀመሪያ ህዝቡን በጎሳ ክልል የሚገድቡትን፣ ሁለተኛ የደቡብ አፍሪቃን ህዝብ በጎሳ የሚከፋፍሉትን፣ ሶስተኛ ትምህርትን ከዘር ጋር የሚያያይዘውን እና አራተኛ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስን የሚገድቡትን ነበሩ። እነኝህ አንገብጋቢ የትግል ስልቶችን ህዝቡ ስላወቃቸው መላውን ደቡብ አፍሪቃን አጥለቀለቁት።

የሃገር አቀፉ ትግል ሲፋፋምም የተለያዩ ድርጅቶች በይበልጥ ተቀራርበው መስራት አማራጭ የሌለው ስለሆነ የደቡብ አፍሪቃ የህንዶች ድርጅት፣ የደቡብ አፍሪቃ ክልሶች ማህበር የህብረት ሸንጎን የጋራ ስምምነት ተፈራረሙ። ይህም የነፃነት ሰንድ የሚከተሉትን መሰረታዊ ሃሳቦች ያጠቃለለ ነበር።

- የህዝብ የበላይነትን ያረጋገጠ መንግስት እንዲቋቋም
- መሬት ያለ አድሎ ለሁሉም እንዲዳረስ
- ሁሉም አፍሪቃውያን አድሎ ሳይደረግባቸው የመኖሪያ ቦታ እንዲያገኙ፤ ስራ እንዲይዙ፣ ፀጥታቸውና ሰላማቸው እንዲረጋገጥ
- ደቡብ አፍሪቃ የሁሉም አፍሪቃውያን ሃገር መሆኗን ማረጋገጥ

የደቡብ አፍሪቃ መንግስት ግን ይህንን ስምምነትና የተፈረመውን ሰነድ የኮሚኒስቶች ሴራ ነው ብሎ ካወጀ በሗላ ድርጅቶቹን በህጋዊ መንገድ እንዳይንቀሳቀሱ አገደ። መሪዎቹን እና ታዋቂ አባላቱን ከእስር ቤት አጎረ። ቀጥሎም መጀመሪው ዙር ላይ ያልታከሉ አፍሪቃውያን ሴቶች የዘር መለያ መታወቂያ እንዲይዙ ታዘዘ። የጥምሩ ጉባኤም የይለፍ መታወቂያን ተቃውሞ ሰልፍ ጠራ። ህዝቡም መታወቂያውን ሳይዝ ፖሊስ ጣቢያ እየሄደ እንዲታሰር የተደረገውን ጥሪ ተቀብሎ ወደ ህዝብ አደባባዮችና ወደ ፖሊስ ጣቢያዎች ጎረፈ። በየአካባቢው ህዝቡ ግልብጥ ብሎ ወጣ። በስፋት የወጣው ህዝብ የደቡብ አፍሪቃን መንግስት ስላስደነገጠው የነጭ ፖሊሶች በሰላማዊ ህዝብ ላይ ሻርፕቪል (Sharpville) ከተባለ ቦታ ተኩስ ከፍተው 69 ሰዎች ሲሞቱ 186 ሰላማዊ ሰዎች ቆሰሉ። ከዚህ እልቂት በሗላ ሰላማዊ ትግሉ አበቃ። ከ49 አመታት በሗላ ማለትም በ1961 ኢ.አ የአፍሪቃ ሁለገብ ጉባኤ ሁለ ገብ ትግልን አወጀ። የባኤው ይፋና ህጋዊ እንቅስቃሴም ከዚያን እለት በሗላ አበቃ። ሸንጎውም ህዝቡን ለመከላከል እንዲችል ነፃነትና ዲሞክራሲ ለመከላከል የትጥቅ ትግል እንደሚያካሂድ ይፋ ሆነ።

በተከታታዩ 18 ወራት ስርአቱን የሚጎዱ 200 ሽምቅ ጥቃቶች ተካሄዱ፡፡ ጥቃቶቹም ያተኮሩት በዘረኛው መንግስት የመገናኛ፣ የፕሮፓጋንዳ፣ የፋይናንስና መሰል አውታሮች ላይ ሲሆን ህዝቡን እንዳይጎዳው ትልቅ ጥንቃቄዎች ይደረጉ ነበር፡፡ መንግስትም ጭፍን ግድያውን፣ እስራቱን፣ ማስጨነቁንና መግደሉን አፋፋመ፡፡ ትግሉ እንደዚህ በተፋፋመበት ወቅት የጉባኤው አመራር ማለትም ኦሊቨር ታምቦና (Oliver Tambo) ጆ ስሎቮ (Joe Slovo) ትግሉን ለመምራት እንዲችሉ ከደቡብ አፍሪቃ በድብቅ ወጡ፡፡ ሌሎችም እንደ ኔልሰን ማንዴላና (Nelson Mandela) ሁሉ የውትድራና ትምህርት ለማግኘት እንዲችሉ ወደ ተለያዩ አጎራባችና ራቅ ያሉ አገሮች ተሰደዱ፡፡ ኢትዮጵያም ለደቡብ አፍሪቃ የነፃነት ትግል ያበረከተችውን፣ ኔልሰን ማንዴላ «ረዥም የነፃነት ጉዞ» ባሉት መፅሃፋቸው ጠቅሰውታል፤ የመጀመሪያ የውትድርና ትምህርታቸውን የተቀበሉት ሆለታ እንደሆነና የመጀመሪያ ሹጉጥም በሽልማት የተሰጣቸው ከኢትዮጵያ መንንስግት ተወካይ መሆኑን በሰፊው አብራርተው ፅፈዋል፡፡ በሂላም በብዙ የአፍሪቃ ፣ የእስያ እንደዚሁም ሌሎች አገሮች ሲንቀሳቀሱ የኢትዮጵያን ፓስፖርት ይጠቀሙ እንደነበሩ ይገልፃሉ፡፡

ሽንጎው ሁለገብ ትግል ለማካሄድ እንደወሰነ ቅዲሚያ የሰጣቸው እንቅስቃሴዎች፡-

- በጠላት ኤላማዎች ላይ ያተኮረ የትጥቅ ትግል ማካሄድ
- የህዝብ እንቅስቃሴን ማፋፋም
- የድርጅቱን መዋቅር በስፋትና በጥልቀት ማስፋፋት
- ከተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታት ድጋፍ ማሰባሰብ ነበሩ፡፡

ትግሉንም ከውስጥ ሆነ ለመምራት እንዲችሉ ኔልሰን ማንዴላ በድብቅ ወደ ደቡብ አፍሪቃ ተመለሱ፡፡ ወዲያው በ1962 ኣ.እ ተይዘው ለፍርድ ቀረቡ፡፡ ክሳቸውም ስርአቱን በሃይ ለመለወጥ እንደሚሞክሩና የኮሚዩኒስት ስርአት ለማቋቋም እንደወሰኑ የሚወነጅል ነበር፡፡ ከዚያም እራሳቸውን ፍርድ ቤት ተከላክለው የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው የረዥም ጊዜ የእስራት ዘመናቸውን ለመጀር ሮቢን ደሴት ተወሰዱ፡፡ በእስር በነበሩበት ጌዜ ከጠባቂ ወታደሮችም ሆነ አብረዋቸው ከታሰሩት አባሎቻቸው ጋር እንዲነጋገሩ አይፈቀድላቸውም ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉም ድንጋይ ሲፈልጡ ለ17 አመታት በአስከፊ እስራት እንዲሰቃዩ ተደረገ፡፡ ማንዴላ ቢታሰሩም የህብረቱ ትግል ግን የባሰ ተጠናከረ እንጂ አልተዳከመም፡፡ በሃገር ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ የሚመሩት አካላት ህዝቡን እያደራጁ ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን አካሄዱ፡፡ ጥቁሮች አፍሪቃውያን በነጩ ነጋዴ ላይ የኤኮኖሚ ማእቀብ ማድረጉን አፋፋሙት፡፡ እቃ ከነጮች ሱቅ መግዛቱን አቆሙ፡፡ የጥቁር ሱቆች፣ ጥቁሮች በሚኖሩበት አካባቢዎች ተቋቋሙ፡፡ ሱቆቹም በተመጣጠነ ከተቻለም በአነስተኛ ዋጋ ለአፍሪቃውያኑ እቃዎችን ማቅረብ ጀመሩ፡፡ የመብራት እና የቤት ኪራይ አንከፍልም አሉ፡፡ ግብር መክፈልም አቋረጡ፡፡ ወሬ አቀባይ አፍሪቃውያንም ላይ እርምጃ መውሰዱ ተፋፋመ፡፡ የታጠቀው አካልም የነጮችን ስርአት የሚጎዱ እርምጃዎችን መውሰዱን አጠነከረው፡፡ የሃይል ማመንጫ፣ የመንግስት ፕሮፓጋንዳ አካላትና ተመሳሳይ ድርጅቶች ተከታታይ እርምጃዎች ተወሰደባቸው፡፡ በጠቅላላው ደቡብ አፍሪቃ በቀድሞው ሁኔታ የማትገዛ አገር መሆኗ ግልፅ እየሆነ መጣ፡፡ የመከላከያ ጥቃቱ ሲፋፋምም የመንግስት አስከፊ እርምጃዎችም ተጠናከሩ፡፡ አፍሪቃውያን በገፍ ይረሸኑ፣ ይታሰሩ፣ ይሰቃዩ ጀመር፡፡ የአገሪቱ የመንግስት መዋቅር እየተዳከመ መሄዱን ያዩ ሃብታም ነጮች እና የውጭ ባለሃብቶች ደቡብ አፍሪቃን እየለቀቁ መኮብለል ጀመሩ፡፡ የአለም መንግስታት ማህበር ታላላቅ መንግስታት አቋምም ለውጥ እያሳየ መጣ፡፡

በትግሉ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በአለም ሁኔታ መለዎጥ የተወጠረው ግንኙነት ከአፍሪቃ ሃገራዊ ጉባኤ አመራር አካላት ጋር ምስጢራዊ ውይይት ጀመረ፡፡ ምስጢራዊ ውይይት ወደ ይፋ ውይይት ተቀይሮ ዘረኛው መንግስት ከአፍሪቃውያኑ ጋር መደራደር ተጀመረ፡፡ ለድርድሩ እንዲያመችም ሮቢን ደሴት ታስረው የነበሩት ማንዴላና ሌሎች አባሎቻቸው ወደ ጆሃንስበርግ ተዛወሩ፡፡ በመጨረሻም፣ ድርድሩ የሚከተሉት ስምምነቶች ላይ ደረሰ፡፡

- የአፍሪቃ ሃገራዊ ጉባኤ ህጋዊ ሆኖ በይፋ መንቀሳቀስ እንዲችል
- ሁሉን ኣቀፍ የሆነ የሽግግር መዋቅር እንዲቋቋምና የሽግግር ህገ መንግስት እንዲነደፍ
- የሽግግሩ ጊዜ ካለፈ በሂላ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲደረግ
- በሃገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ሰማስፈን እንዲረዳ የእርቅና የሰላም ኮሚሽን ተቋቁሞ ለደረሰው ጥቃት መፍትሄ እንዲፈልግና በስራ ላይ እንዲያውል

ከዚያም የደቡብ ኣፍሪቃ ሃገራዊ ጉባኤ ህጋዊ እንዲሆን ስምምነት ላይ ስለተደረሰ ሸንጎውና ያቀፋቸው ድርጅቶች በነፃ ተወዳድረው የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ መንግስ በ1994 ኣ.እ ሲቋቋም ኔልሰን ማንዴላም የመጀመሪያው የዲሞክራሲያዊ ደቡብ ኣፍሪቃ ፕሬዜዳንት ሆነው ተመረጡ፡፡ ይኸው እንግዴህ ላለፈው 13 ኣመታት ደቡብ ኣፍሪቃን  የኣፍሪቃ ሃገራዊ ጉባኤ እየመራ ዲሞካራሲ ግንባታው ቀጥሏል፡፡

ኣሁን ኢትዮጵያ የተዘፈቀችበት የመከራ ጊዜ ከደቡብ ኣፍሪቃ መራራ ዘመን ጋር ተመሳሳይነት ኣለው፡፡ ስለዚህ፣ «ለኢትዮጵያ የቆምን ነን!» የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ድርጅቶች ከዚህ የደቡብ ኣፍሪቃውያን የነፃነት ትግል ብዙ መማር ይችላሉ፡፡